# የሰባት ቤት ጉራጌ የለቅሶ ቃል-ግጥም ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ትንተና

ጌታቸው ዳዊ[1]

**አጠቃሎ**

ኢትዮጵያዊያንን አንድ ከሚያደርጉ በርካታ የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የለቅሶ ሥርዓት ሲሆን ክዋኔውና ማህበራዊ ፋይዳው ግን እንደ ህዝቡ ተጨባጭ ሁኔታ የተለያየ ገጽታ አለው፡፡ በሰባት ቤት ጉራጌ ዘንድ ታዋቂ ሰዎች ሲሞቱ በቃል-ግጥም ታጅቦ የሚፈፀም የለቅሶ ሥርዓት "የቋም ብኜ" (የቁም ለቅሶ) ይባላል፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ክዋኔና ፋይዳ መተንተን ነው፡፡ ቃል-ግጥሞቹ የተሰበሰቡት በተፈጥሯዊ ዐውዳቸው ነው፡፡ የመሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ነበሩ፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ክዋኔና ፋይዳ የተተነተነው ከብሔረሰቡ ዕውቀት እና ምሁራን ካዳበሯቸው ቲዮሪዎች አኳያ ነው፡፡ ክዋኔ ማለት ቃል-ግጥሞች የተነገሩበትና የቀረቡበት ስልት ሲሆን ማህበራዊ ፋይዳ ደግሞ ቃል-ግጥሞቹ በመከወናቸው ምክንያት ማህበረሰቡ የሚያገኘው ጠቀሜታ/አገልግሎት ማለት ነው፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክዋኔና ፋይዳ በጊዜ ሒደት እየተለወጠ የሚሔድና ቀጣይነት ያለው ባህርይ ይታይባቸዋል፡፡ በመሆኑም የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ክዋኔና ፋይዳ በየዘመኑ ከሚደረስበት አስተሳሰብና ፍላጎት ጋር በተስማማ ሁኔታ ጠብቆ ለማቆየት ጥናትና ምርምር ማከናወን፤ መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀትና መተንተን የማስተዋወቅና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡

## 1. መግቢያ

አገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ ከነዚህም አንዱ የጉራጌ ብሔረሰብ ነው፡፡ ብሔረሰቡ የሚገኘው በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ሰሜናዊ ክፍል ሲሆን መልክዐ-ምድራዊ አቀማመጡ ደግሞ መካከለኛው የሸዋ ፕላቶ ላይ ነው፡፡ ታሪካዊና መልክዐ-ምድራዊ ሁኔታዎች የጉራጌ ብሔረሰብ መለያ የሆኑ ልዩ ልዩ መገለጫዎችን ፈጥሯዋል፡፡ ከነዚህም መካከል የብሔረሰቡ የሀዘን መግለጫ ሥነ-ሥርዓትና የለቅሶ ቃል ግጥሞች ይገኙበታል፡፡

ከልደት በኋላ ያሉት የሰው ልጅ የህይወት ምዕራፎች መቋጫቸው ህልፈተ ህይወት ነው፡፡ በዚህ የሰው ልጅ የህይወት መጨረሻ ምዕራፍ ላይ እንደየ ባህሉ ሁኔታ ቋሚው ለሟች ወገኑ ሀዘኑን ይገልፃል፡፡ የሰው ልጅ ወገኑ በመሞቱ የተሰማውን ሀዘን ከሚገልጽባቸው ስልቶች አንዱ ሟችን ቃል-ግጥም መግለጽ ነው፡፡ በሰባት ቤት ጉራጌ ዘንድም በተመሳሳይ ሁኔታ በቃል-ግጥም ታጅቦ የሚከወን ሥርዓተ ለቅሶ አለ፡፡ ይህም *"የቋም ብኜ"* (የቁም ለቅሶ) ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ጥናት

[1] በ ፎክሎር ጥናት ፒ.ኤች.ዲ getachewdawi@yahoo.com

መልካም ምግባር ያላቸው ወንዶች ሲሞቱ በሚፈጸም የቁም ለቅሶ ወቅት በሚከወኑ ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

ጥናቱ በአምስት ክፍሎችና በሀያ አራት ንዑሳን ርዕሶች የተደራጀ ነው፡፡ ክፍል አንድ የጥናቱ አካባቢ ዳራ፣ የጥናቱ ጥያቄዎች፣ ዓላማዎች፣ የጥናቱ ዓይነትና ወሰን የያዘ ነው፡፡ ክፍል ሁለት የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ የሆኑት የፎክሎር፣ የስነቃልና የቃል ግጥም ትርጓሜዎችን እንዲሁም የመረጃ መሰብሰቢ ዘዴዎችን የመተንተኛ ቲዮሪ ይዟል፡፡ ክፍል ሦስት የለቅሶ ቃል ግጥሞች ክዋኔ፤ ክፍል አራት የለቅሶ ቃል ግጥሞች ማህበራዊ ፋይዳ እንዲሁ ክፍል አምስት የቃል ግጥሞቹ ለውጥና ቀጣይነት ቀርበዋል፡፡

በጥናቱ ከተካተቱት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚ የሆነው ጥናቱ የተካሔበትን አካባቢያዊ ዳራ የሚገልጹ መረጃዎች ከዚህ በመቀጠል ቀርበዋል፡፡

## 2. የጥናቱ ዳራ

### 2.1. የጥናቱ አካባቢ

“ጉራጌ” የሚለው ስም ብሔረሰቡንና ብሔረሰቡ የሚኖርበትን አካባቢ የሚገልጽ መጠሪያ ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል 1991:7 ዓ.ም[2])፡፡ ነገር ግን የስሙ መነሻ ምን እንደሆነ የሚያብራራ በጉራጌኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኝ የስነ-ልሳን ትርጓሜ ስለመኖሩ የተመዘገበ የጽሑፍ መረጃ የለም፡፡ [3] የጉራጌ ብሔረሰብ የሰፈረው የማዕከላዊ ደቡብ ኢትዮጵያ ክፍል በሆነው በሸዋ “ፕላቶ” ደቡባዊ ምዕራብ ላይ ነው፡፡

የመሬቱ መልክዓ-ምድራዊ ወሰን (Physical Boundary) የኦሞ፣ የጊቤና የአዋሽ ተፋሰሶችንና የስምጥ ሸለቆ ሃይቆችን መሰረት አድርጎ የተፈጠረ ነው፡፡ በምስራቅ በኩል ከስምጥ ሸለቆና ከዝዋይ ሃይቅ ጋር ይዋሰናል፡፡ የጊቤን ወንዝ ምስራቃዊ ዳርቻ ተከትሎ ያለው ሰፊ ረባዳ መሬት ምዕራባዊ ወሰን ነው፡፡ የአዋሽ ወንዝ ደግሞ ሰሜናዊ ወሰን ሲሆን የከንባታ የተራራ ሰንሰለቶች ደቡባዊ ወሰን ናቸው (Shack [4] 1966:31፤ ሰይፉ 1966:8-10 ዓ.ም፤ lpcar 1970)፡፡ ዞኑ አራት ዋና ዋና የአየር ንብረት ክፍሎች አሉት፡፡ ይሄውም ውርጭ (4.1%)፣ ደጋ (27.5%)፣ ወይና ደጋ (65.5%) እና ቆላ (3.1%) ናቸው፡፡ የጉራጌ መሬት ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ ከ1000 ሜ. (የጊቤ ሸለቆ) እስከ 3600 ሜ. (ዘቢዳር ተራራ) ይደርሳል (Muluneh 1994: 35፤ Shack 1966:31)፡፡

---

[2] በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመታት “ዓ.ም” በሚል ካልተለዩ በስተቀር የተፃፉት በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ነው፡፡

[3] ይህ ጥናት በሚካሔድበት ጊዜ መረጃ አቀባይ አዛውንቶች ስያሜው በጉራግኛ ቋንቋ ምን ማለት እንደሆ እንዲገልጹ ተጠይቀው ነበረ፡፡ ከጥንት ጀምሮ ህዝቡ ሲጠቀምበት የመጣ መጠሪያ መሆኑን ከመግለጽ በስተቀር አፈታሪክን መሰረት ያደረገ ማብራሪያ መስጠት አልቻሉም፡፡

[4] በዚህ ጥናት ውስጥ በእንግሊዝኛ የጻፉ የውጭ ሀገር ሰዎች ስም እንዳለ ተወስዷል፡፡

የብሔረሰቡ ባህላዊ ወሰንን (Cultural Boundary) ብንመለከት በሰሜን በኩል ክርስቲያኑ ንጉሳዊ ግዛት ጋር ይዋሰን ነበር፡፡ በዚህ አቅጣጫ የተመሰረተው ግንኙነት በሰሜናዊው የጉራጌ ሕዝብ (ክስታኔ) ባህል ላይ ተጽዕኖ አሳርፏል፡፡ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ማሕበረሰቦች (የም፣ ቀቤና፣ ሀድያና ከምባታ) ደግሞ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አቅጣጫ ያዋስኑታል፡፡ ከእነዚህ ማህበረሰቦች ጋር የተፈጠረው መስተጋብር በሰባት ቤት ጉራጌ ላይ ተጽዕኖ አሳርፏል (Leslau 1952:63-81፤ Markakis 1966:58-59)፡፡አሁን ያለውን አስተዳደራዊ ወሰን ስንመለከት የጉራጌ ብሔረሰብ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ሰሜናዊ ክፍል ይገኛል፡፡ ከ1987 ዓ.ም [5] ጀምሮ አስተዳደሩ በዞን ደረጃ የተዋቀረ ነው፡፡ ዞኑ በሰሜን፣ በምስራቅና በምዕራብ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በደቡብ ምዕራብ ከየም ልዩ ዞን፣ በደቡብ ምስራቅ ከስልጤ ዞን፣ በደቡብ ደግሞ ከሀድያና ስልጤ ዞኖች ጋር ይዋሰናል፡፡ የዞኑ የቆዳ ስፋት [6] 5,893 ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን አስተዳደራዊ መዋቅሩም በ16 ወረዳዎችና በ5 የከተማ መስተዳድሮች የተደራጀ ነው፡፡ በ16ቱ ወረዳዎችና በ5ቱ የከተማ መስተዳድሮች ውስጥ በጠቅላላ 437 የቀበሌ መስተዳድሮች ይገኛሉ፡፡ የዞኑ ዋና ከተማ ወልቂጤ ሲሆን ከአዲስ አበባ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በጅማ መንገድ ላይ በ 153 ኪ. ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የጉራጌ ዞን በክልሉ ከሚገኙና ከፍተኛ ህዝብ ከሰፈረባቸው ዞኖች አንዱ ነው፡፡

የኢትዮያ ፌደራል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን (1999:17 ዓ.ም) ሪፖርት እንደሚያሳየው የብሔረሰቡ ብዛት 1.9 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1.2 ሚሊዮን በገጠር፣ 792,000 ደግሞ በከተማ የሚኖር ነው፡፡ በዞኑ ከሚኖረው ህዝብ መካከል 51% ሰባት ቤት ጉራጌ፣ 20% ሶዶ ጉራጌ፣ 17% መስቃንና ማረቆ (ሊቢዶ)፣ 10% ቀቤና ሲሆን አማራና ሌሎች ደግሞ 2% ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ልዩነት ቢኖርም የኑሯቸው መሰረት ተመሳሳይ ነው፡፡

የብሔረሰቡ ኑሮ የተመሰረተው "በቅይጥ" ግብርና ላይ ነው፤ እርሻ ያርሳል፣ እንስሳትም ያረባል፡፡ በተለይ እንሰት [7] በስፋት ስለሚተከል ከግማሽ በላይ የሚሆነው የዞኑ መሬት በእንሰት የተሸፈነ ነው፡፡ የእንሰት ተክል ሽፋኑ ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ በደጋማ አካባቢዎች 51% ሲሆን በወይና ደጋ አካባቢዎች ደግሞ እስከ 65% ይደርሳል (Muluneh 1994 181)፡፡ የእንሰት ተክል ከብሔረሰቡ ባህልና አስተሳሰብ ጋር ያለውን ቁርኝት ሲገልጹ Shack (1966:55) "... intensively cultivated, and a complex of cultural traits has evolved connected with its mode of production [*Enset*] dominates Gurage mode of thought and interest, and moulds their livelihood" (እንሰት በስፋት ስለሚተከል ከስልተ ምርቱ ጋር ተያይዘው የተፈጠሩ ውስብስብ ባህላዊ መገለጫዎች የጉራጌዎችን አስተሳሰብና ፍላጎት የተቆጣጠሩና የኑሯቸውንም መሰረት የወሰኑ ናቸው) በማለት ጽፈዋል፡፡


---

[5] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዲሪ) እና ክልሎች የተመሰረቱበት ጊዜ ነው፡፡

[6] በጉራጌ ዞን 260 ሰዎች በአንድ ስኴር ኪሎ ሜትር መሬት ላይ ይኖራሉ፡፡ የአንድ ቤተሰብ አማካይ ይዞታ 0.5 በመሆኑ የመሬት ይዞታው የተጣበበ ነው (Gurage Development Program: (GDP) 1998: 3 ዓ.ም)፡፡

[7] የእንሰት እርሻ በአገር አቀፍ ደረጃ 132,834 ሔክታር መሬት እንደሚሸፍንና 20% (10-15 ሚሊዮን) የሚሆነውን ህዝብ እንደሚቀልብ ጥናቶች ያሳያሉ (ሰይፉ 1993ዓ.ም፤ Muluneh 1994፡178)፡፡

በብሔረሰቡ ዘንድ ያለውን የዘዬ ልዩነት መሠረት በማድረግ ምሁራን ጉራጌን የሰሜን ጉራጌ (ክስታኔ) እና የምዕራብ ጉራጌ (ሰባት ቤት) በማለት ይከፍሉታል፡፡ ይህ ጥናት የሚያተኩረው በሰባት ቤት (በምዕራብ) ጉራጌ ላይ ነው፡፡ ሰባት ቤት ለምን፣ እንዴትና መቼ እንደተመሰረተ ከዚህ በመቀጠል ቀርቧል፡፡




ስዕል 1. የጉራጌ ዞን ካርታ፡- በክልል፣ በዞን በወረዳ ደረጃ

## 2.2. ሰባት ቤት ጉራጌ

የሰባት ቤት ጉራጌ ህብረት ከመመስረቱ በፊት የአምስት ቤት ጉራጌ የሚባል ህብረት ነበረ፡፡ ህብረቱ በሒደት ሁለት አዳዲስ አባላትን በማካተት ወደ ሰባት ቤት ጉራጌ ህብረትነት [8] አድጓል፡፡ የሰባት ቤት ጉራጌ ህብረት የተመሰረተው አባላቱን ከውስጥ ግጭትና ከውጭ ጥቃት ለመከላከል

[8] ህብረቱን በመፍጠርና የጋራ ደህንነትን በማረጋገጥ ረገድ በዘመኑ የነበሩ የየክፍለ-ህዝቡ መሪዎች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ የመስራች አባቶች ገድሎች እንደየደረጃቸውና እንደየስኬታቸው በጎሳና በብሔረሰብ ደረጃ በሚከወኑ ቃል-ግጥሞች ይወደሳሉ፡፡

ነበር፡፡ ነገር ግን የሰባት ቤት ጉራጌ ህብረት የተመሰረተበት ጊዜን፣ ወደ ህብረቱ የተቀላቀሉ ሁለቱ ህዝቦች ማንነትንና የጠቅላላ አባላቱን ማንነት በሚመለከት የሚቀርቡ መረጃዎች የተለያዩ ናቸው፡፡

ህብረቱ የተመሰረተበትን ጊዜ በሚመለከት ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች አሉ፡፡ አንደኛው ዓለማየሁ ነሪ (1985:59 ዓ.ም) የመስራች አባቶችን እድሜ በማስላት ህብረቱ የተመሰረተው በ1690ዎቹ ነው በማለት ጽፈዋል፡፡ ሁለተኛ Shack (1966:4) ህብረቱ ተመሰረተው ከምኒልክ ወረራ (1882) በኋላ ነው ይላሉ፡፡ ህብረቱ የተመሰረተው ከዳግማዊ ምኒልክ ወረራ በፊት ስለመሆኑ በሌላ ቦታ ተጽፎ እናገኛለን (ወርቁ 1983:20፤ 1995:25 ዓ.ም)፡፡ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች በተጨማሪ የሰባት ቤት ጉራጌ አባላት ማንነት ላይ የሚቀርቡ መረጃዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ የጉመር፣ የኤነርና የመገር ህዝቦች በህብረቱ ውስጥ የነበራቸው ቦታና ውክልና ግልጽ አይደለም፡፡ በብሔረሰቡ አፈታሪክና በብዙ በጥናቶች ተጠቅሰው የሚገኙት የህብረቱ አባላት ቸሀ (ጉመርን ጨምሮ)፣ እነሞር (ኤነርንና መገርን ጨምሮ)፣ እገ፣ ጌቶ፣ ምሁር፣ እንደጋኝና መቆርቆር ናቸው፡፡

የሰባት ቤት ጉራጌ ካሉት ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች መካከል አንዱ ታዋቂ ሰዎች ሲሞቱ የሚከወነው ቃል ግጥም ነው፡፡ እስካሁን በብሔረሰቡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ የተካሔዱት ጥናቶችን ይዘት ስንመረምር በቃል-ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ትኩረት አድርጎ የተካሔደ ጥናት አለመኖሩን እንረዳለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቃል-ግጥሞቹ ውስጥ ያሉ ገናነ ማህበራዊ ፋይዳዎችንና የሚታይባቸውን የለውጥና ቀጣይነት ሁኔታ የሚያሳዩ ጥናቶች የሉም፡፡ ይህ ጥናት በየጊዜው በመለዋወጥ ላይ በሚገኘው የሰባት ቤት ጉራጌ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳቸው ይተነትናል፡፡

### 2.3. የምርምር ጥያቄዎች

የሰባት ቤት ጉራጌ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክዋኔና ፋይዳ ላይ የተካሔደው ጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. የሰባት ቤት ጉራጌ ቃል-ግጥሞች ክዋኔ ምን ይመስላል?
2. የቃል-ግጥሞቹ ማህበራዊ ፋይዳ ምንድን ነው?
3. የቃል-ግጥሞች ለውጥና ቀጣይነት የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

### 2.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በመመለስ የሰባት ቤት ቃል-ግጥሞች ክዋኔ መግለጽና ማህበራዊ ፋይዳቸውንም መተንተን ነው፡፡ ዓብይ ዓላማውን ለማሳካት የተነደፉት ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ፡-

1. የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክዋኔ በዐውዳቸው መግለጽ፣
2 የቃል-ግጥሞቹ ማህበራዊ ፋይዳ መተንተንና
3. የቃል-ግጥሞች ለውጥና ቀጣይነት ማሳየት ናቸው፡፡

### 2.5. የጥናቱ ዓይነት

ይህ ጥናት የሰባት ቤት ጉራጌ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ከዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ የሚተነትን በመሆኑ የማህበረሰብ ጥናት (Ethnographic Research) ነው፡፡ ኢትኖግራፊያዊ ጥናት ትኩረት መሰረቱ የሚጠናው ህዝብ ያለውን አገር በቀል እውቀት በሚመለከት የሚሰበሰበው መረጃ ነው፡፡ በመሆኑም የሰባት ቤት ጉራጌ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን በሚመለከት ያለውን እውቀት የሚያስረዱ መረጃዎች በኢትኖግራፊያዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ተሰብስበዋል፡፡ እንደዚሁም የቃል-ግጥሞቹ ከዋኔ የቀረበው "ገላጭ" (Descriptive) ተብሎ ከሚታወቀው ዘዴ አኳያ ሆኖ መሰረቱ "የጥቂም ጥናት" (Case Study) ዘዴ ነው፡፡ ማህበራዊ ፋይዳቸው የተገለጸው ደግሞ "የትንተና ስልት" (Analytical Approach) በሚባለው የጥናት ዘዴ ነው፡፡

### 2.6. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ መልክዓ ምድራዊ ወሰን በሰባት ቤት ጉራጌ ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ከይዘት አንጻር ጥናቱ የሚሸፍነው የቃል ግጥም ዘርፍ ታዋቂ ወንዶች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በሚከወኑ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡

## 3. የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ

ይህ ክፍል የቃል-ግጥም ጥናት በስነ ሰብ ጥናት ውስጥ የሚካተትበትን ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ያብራራል፡፡ የሀገር በቀል ዕውቀትን የሚያጠና ሰፊ ዘርፍ ፎክሎር ይባላል፡፡ ይህ የጥናትና ምርምር ዘርፍ በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.1 ፎክሎር

አንድ ማህበረሰብ ያዳበረውን እውቀት፤ ይህንንም ጠብቆ የሚያቆይበትና የሚያስተላልፍበትን መንገድ ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ሰፊ የጥናት ዘርፍ ፎክሎር ይባላል፡፡ ፎክሎር የአንድ ህዝብ (ፎክ) እውቀት (ሎር) የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ ፎክሎር የሚለው ቃልም *ህዝብና ልማድ* የሚሉ የሁለት ጽንሰ ሀሳባዊ ቃላት ውህድ መሆኑን ተጽፏል (Schoemaker 1990፡3)፡፡ ህዝባዊ የሚለው ቃል የሰዎችን ስብስብ አመላካች ሲሆን ልማድ ደግሞ በባህል ክፍል ውስጥ የሚመደብ ነው፡፡ የሰው ልጅ ማህበራዊ በመሆኑ አንዱ ከአንዱ ጋር በመግባባት ግንኙነት ይፈጥራል፤ ሀገር በቀል እውቀትም የዚህ ውጤት ነው፡፡

በባህል ጥናት ዘርፍ የሚደረግ ምርምርን ስርዓት ለማስያዝና መልክ ለመስጠት ሲሉ Dorson የተባሉ ተመራማሪ ፎክሎርን በአራት ዋና ዋና ምድቦች የከፈሉት መሆኑን ፈቃደ (1998፤ 2-4 ዓ.ም) ይገልጻሉ፡፡ አራቱ ክፍሎች ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ቁሳዊ ባህል ናቸው፡፡ እነዚህ የፎክሎር ዘርፎች አንዱ ሌላውን በሒደት እየቀረጸ የአንድን ህዝብ የጋራ ሀገረሰባዊ እውቀት ለመግለጽ ያገለግላሉ፡፡ እነደዘሁም ፎክሎር የሰው ልጅ የማንነት መገለጫና

የፍላጎት ማስተላለፊያ መንገድ ነው። ቁሳዊ ባህል ደግሞ ቁሳዊ ቅርጹ ሲሆን ስነቃል የዚህ ሞተርና አንቀሳቃሽ ነው። የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ከፎክሎር ዘርፎች አንዱ በሆነው ስነቃል ውስጥ የሚካተት ነው።

ስነቃል የሰው ልጅ እውቀቱን (ፎክሎሩን) ትርጉም የሚሰጥበት፣ እንዲታይና እንዲሰማ የሚያደርግበት፣ ጠብቆ የሚያቆይበትና የሚያስተላልፍበት ስልት ነው። ስነቃል የሰው ልጅ እውቀት በአንደበት አማካይነት የሚገለጽበት እንዲሁም የባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ የሚብራራበት መንገድ በመሆኑ የሰው ልጅ ምኞቱን፣ ፍላጎቱን፣ ችግሩን፣ ደስታውን፣ ሐዘኑን፣ ደግነቱን፣ ተግባሩን ወዘተ... ሁሉ በቃሉ (በአንደበቱ) ይገልጽበታል። ስነቃል ቃል-ግጥሞች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ ቀልዶች፣ አፈታሪኮች እና ሌሎችንም ያያዘ ሲሆን እነዚህ ደግሞ በቃል የሚከወኑ ናቸው። ዘሪሁን (1992፡20) "ስነቃል በመነገር፣ በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነጥበብ ነው" በማለት ያብራራሉ። በቃል-ግጥሞቹ ላይ የሚደረግ ጥናት በስነቃል ጥናት ዘውግ ውስጥ የሚመደብ በመሆኑ ከስነቃል ዘርፎች አንዱ የሆነውን ቃል-ግጥም እንደሚከተለው ተገልጿል።

### 3.2 ቃል-ግጥም ምንድነው?

የሰው ልጆች ለብዙ ዘመናት የአኗኗር ሁኔታቸውን፣ ፍላጎታቸውንና እውቀታቸውን በቃል-ግጥም መግለጽ የጀመሩት ሀሳባቸውን በጽሑፍ መግለፅ ከመጀመራቸው በፊት ነው (ዘሪሁን 1992፤20 ዓ.ም)። ይህ የሆነውም ቃል-ግጥም በቃል የሚከወንና በማስታወስ የሚተላለፍ ያልተጻፈ የግጥም አይነት በመሆኑ ነው። በቃል የሚከወንበት ምክንያት የሚከውነው ማህበረሰብ የጽሑፍ ጥበብ የሌለው ሲሆን ወይም ደግሞ በቃል መከወን ተመራጭ ሆኖ ሲያገኘው ነው ይላሉ Finnegan (1992:119)። በተጨማሪም ፈቃደ (1991:85-86) "...ቃልግጥም ማለት፣ አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረሱ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ሕዝባዊ ግጥም ነው" ይላሉ።

ቃል-ግጥሞች ከአንድ ህብረተሰብ እውቀትና ፍላጎት የሚመነጩና ይህንኑም መልሰው የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ ሲከወኑም ለሚያደምጥ ሰው አዲስ እውቀትና ልምድ ስለሚያስገኙለት ዓለሙን ይበልጥ እንዲገነዘብና እንዲያጤን ያግዙታል። ከቃል-ግጥሞች በሚገኘው እውቀት ህይወትን ይበልጥ ለመገንዘብ የሚቻለው አድማጩ ያገኘውን እውቀት ከራሱ የህይወት ተሞክሮና ከማህበረሰቡ ልዩ ልዩ እሴቶች ጋር እያዋሀደ ያጤነው እንደሆነ ነው (ዘሪሁን 1992:74)። ከዚህ አኳያ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ይበልጥ ለመገንዘብ የሚቻለው ሰበበ ድርሰታቸውን፣ ባህሪያቸውን፣ ይዘታቸውን፣ ፋይዳቸውንና የሚከወኑበትን ዐውድ በአንክሮ በማጤን ነው።

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የብሔረሰቡን የሀዘን መግለጫ ሥርዓት የሚያሳዩ “ህዝባዊ ግጥሞች” ናቸው፡፡ በዚህም ብሔረሰቡ ቃል-ግጥሞቹን የሚከውነው የህይወት ፍልስፍናውን ጠብቆ ለማቆየትና ለማስተላለፍ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ስለዚህ ቃል-ግጥምን በሚመለከት ምሁራኑ የሰጧቸው አጠቃላይ ትርጓሜዎችና የብሔረሰቡ እውቀት የዚህ ጥናት ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ናቸው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለማህበረሰብ ጥናት ግብዓት የሚሆን መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ለጥናቱ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጠቃሚ እንደሆኑ በመስኩ ምሁራን (Goldestein 1964፤ ፈቃደ 1991፡122-124 ዓ.ም) የተገለጹት የሚከተሉት ዘዴዎች ለዚህ ጥናትም መረጃ ለመሰብሰብ አገልግለዋል፡፡

**ምልከታ፡-** በዚህ ጥናት ውስጥ ምልከታ ማለት የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ በተከወኑበት ተፈጥሯዊ ዐውድ (ቦታና ጊዜ) ተገኝቶ መረጃ የተሰበሰበበት ሁኔታ ማለት ነው፡፡ ቃል-ግጥሞች በተፈጥሯዊ ዐውዳቸው ሲከወኑ መረጃ የተሰበሰበው በለቅሶ ቦታ በመገኘት ነበር፡፡ ዘዴው ተግባራዊ የተደረገውም ክዋኔውን አስተውሎ በመመልከትና ቃል ግጥሞችንም በጥሞና በማድመጥ ነበር፡፡ ቃል-ግጥሞች በተፈጥሯዊ ዐውዳቸው ሲከወኑ ለመመልከት የተቻለው በጉመር ወረዳ ውስጥ ልዩ ስሙ የግንድ ተብሎ በሚጠራ ቦታ አጋዝ ህትት ላጫ [9] የተባሉ ታዋቂ ሰው የካቲት 29/2008 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በዚህ ለቅሶ ላይ በመገኘት ታዋቂ ሰዎች ሲሞቱ የሚገጠሙ ቃል-ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡

**ቃለ መጠይቅ፡-** የቃል-ግጥሞችን ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ በተሻለ ሁኔታ የሚያውቁ አዛውንቶችን በመጠየቅ መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ ነው፡፡ በምልከታ ግልጽ ያልነበሩ ክዋኔዎችን ውስን የቃለ መጠይቅ ዘዴን በመጠቀም ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት ተችሏል፡፡ ብሔረሰቡ ስለ ለቅሶ ቃል-ግጥሞች ያለውን እውቀት ለመገንዘብ ይህ ዘዴ ጠቃሚ ነበር፡፡ በነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ቀጥሎ ከቀረቡት የቲዮሪ እሳቤዎች አኳያ ተተንትነዋል፡፡

## 3.4 መረጃ መተንተኛ ቲዮሪዎች

ቃል-ግጥሞችን በሚመለከት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች የመስኩ ምሁራን “ኤቲክ” (Etic) እና “ኤሚክ” (Emic) ብለው ከሚጠሯቸው ቲዮሪዎችና እሳቤዎች አንፃር ተተንትነዋል፡፡ “ኤቲክ” ቲዮሪ ማለት ምሁራን ያዳበሯቸው እሳቤዎችን የሚያመለክት ሲሆን መረጃዎችም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡ የ“ኤሚክ” ቲዮሪ እሳቤዎች ደግሞ ቃል-ግጥሞችን ከብሔረሰቡ እውቀት አኳያ መተንተን ማለት ነው፡፡ ምሁራን ያዳበሯቸው “ኤቲክ” ቲዮሪዎች

[9] የአጋዝ ህትት ቤተሰቦች የለቅሶውን ሥነ ሥርዓት ፎቶ ለማንሳትና በቪዲዮ ለመቅረጽ ፍቃደኞች ስለነበሩ የተገኘው መረጃ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

እዚህ ጋር ለብቻቸው ከመዘርዘር ይልቅ በነዚህ እሳቤዎች የሚተነተኑ ርዕሰ ጉዳዮች በሚቀርቡበት ክፍል ሦስት ሥር ማቅረቡ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለምሳሌ የቃል-ግጥሞቹ ክዋኔ በቀረበበት ክፍል ሦስት ውስጥ ስለ የክዋኔ ቲዮሪ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ የ"ኤሚክ" ቲዮሪ እሳቤ ግን ለብቻው እዚህ ጋር ተብራርቷል፡፡ ቲዮሪው የሚያጠነጥነው አንድ ህዝብ ስለ ባህሉ ባለው እውቀት ላይ በመሆኑ በዋና ዋና የጥናቱ ክፍሎች ውስጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም እሳቤው የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ክዋኔ ለመግለጽና ማህበራዊ ፋይዳቸውንም ለመተንተን አስፈላጊ ነው፡፡ ቃል ግጥሞቹ ከብሔረሰቡ እውቀት አኳያ የተተነተነበት የ"ኤሚክ" ቲዮሪ ጽንሰ ሀሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**"ኤሚክ"(Emic) ቲዮሪ፡-** የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን በሚመለከት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች የመስኩ ምሁራን "ኤሚክ"[10] ብለው ከሚጠሩት የቲዮሪ እሳቤ አንፃር ተተንትነዋል፡፡ የቲዮሪው ዋነኛ ሀሳብ የሚያጠነጥነው ባህላዊ ክዋኔዎችን ከህዝቡ እውቀት አኳያ የማጥናት አስፈላጊነት በማጉላት ላይ ነው (Ben-Amos 1982)፡፡ በመሆኑም የ"ኤሚክ ቲዮሪ" ጽንሰ ሀሳብ የተመሠረተው በሀገረሰባዊ እውቀት ላይ ነው፡፡ አንድን ባህላዊ ክዋኔ ከዚህ ቲዮሪ አኳያ ማጥናት ማለት የባህሉ ባለቤቶች የባህልና የፈጠራ ውጤቶቻቸውን የሚያበጁበት፣ የሚከፋፍሉበት፣ የሚያደራጁበትና የሚተነትኑበት መስፈርት መሰረት በማድረግ ማጥናት ነው፡፡

ከ"ኤሚክ ቲዮሪ" አንጻር የሚካሔዱ ጥናቶች ባህል-ውሱን ናቸው፡፡ ለምሳሌ በጀርመን ወይም በናይጄሪያ ባህል ያሉ የቃል-ግጥም ዓይነቶች የሚደራጁበትና የሚተነተኑበት ስልት የአማርኛ ወይም የጉራጌኛ ቃል-ግጥሞችን ለማደራጀትና ለመተንተን አያገለግልም፡፡ ይህን ሀሳብ ብርሃኑ (1999:350 ዓ.ም) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡ "የሥነ-ግጥም ጥናትና ትንታኔ መሰረት የሚያደርጋቸው እሳቤዎችና መመዘኛዎች ከዚያው ከተጠኚው ባህል የፈለቁና በዚያው ሥራዎቹ ከበቀሉበት ማህበረ-ባህላዊ አካባቢ የመነጩ መሆን [አለባቸው]"፡፡ በዚህም የኤሚክ ቲዮሪ መሰረቱ አገረሰባዊ እውቀት መሆኑን እንረዳለን፡፡ አንድን ባህላዊ ክዋኔ ከኤሚክ ቲዮሪ አኳያ መተንተን ማለት የባህሉ ባለቤቶች የባህልና የፈጠራ ውጤቶቻቸውን የሚያበጁበት፣ የሚረዱበት፣ የሚያደራጁበትና የሚተነትኑበት መስፈርት መሰረት በማድረግ የሚካሔድ ትንተና ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ከኤሚክ ቲዮሪ አንጻር የሚካሔዱ ትንተናዎች ውጤት ባህል-ውሱን ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህን እሳቤ መነሻ በማድረግ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ማጥናት ማለት ብሔረሰቡ ስለ ቃል-ግጥሞቹ ያለውን እውቀት ማጥናት ማለት ነው፡፡

## 4. ክዋኔ

የቃል-ግጥሞችን ክዋኔ ከማየታችን በፊት በዚህ ጥናት ውስጥ ክዋኔ ምን ማለት እንደሆነ አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት ጠቃሚ በመሆኑም ምሁራን ስለ ክዋኔ ከሰጧቸው ጽንሰ ሀሳባዊ

[10] የ‹ኤሚክ› ቲዮሪ ባህላዊ ክዋኔዎችን ከህዝቡ (ፎክ) እውቀት አኳያ ለመተንተን የሚያግዝ አቅጣጫ ነው (Ben Amos 1993)፡፡

ማብራሪያዎች እንጀምራለን፡፡ ከዋኔ[11] ድርጊት በመሆኑ የቃል-ግጥም ከዋኔ ማለት ደግሞ ቃል-ግጥሙ የቀረበበት መንገድ ማለት ነው፡፡ ከዋኔ ሰዎች አንድን ድርጊት የሚፈጽሙበት፣ የሚጋሩበትና ከድርጊቱ ጋር የሚዛመዱበት ስልት በመሆኑ ከሰው ልጅ የእለት ተዕለት ህይወት የሚነጠል ጉዳይ አይደለም፡፡ ሀገር በቀል ዕውቀት ህልውና የሚኖረው ሲከወን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የባህሉ ከዋኞችንና ታዳሚዎችን የሚያካትትና በከዋኔ ውስጥ ያለው ጉዳይም መመዝገብና መተንተን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ከዋኔ የአፋዊ ኪነተ ቃል ህይወት (ፈቃደ 1984:3 ዓ.ም) በመሆኑ ከዋኔ ከሌለ ስነቃል አካላዊ ህልውናና ጥበባዊ ተገላጭነት የለውም (ዘሪሁን 1992:22፤ ብርሃኑ 1995:5 ዓ.ም)፡፡ ከነዚህ ትርጓሜዎች በመነሳት ከዋኔ በልዩ ልዩ ስልቶች የሚገለጽ ጥበብ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችም በልዩ ልዩ የከዋኔ ስልት ይቀርባሉ፡፡ እያንዳንዱ ቃል-ግጥም በራሱ መንገድ የተበጀ የጥበብ ሥራ በመሆኑ የራሱ የሆነ የአከዋወን ስልት ይይዛል (ብርሃኑ 1999:234 ዓ.ም)፡፡

ከላይ በቀረበው የከዋኔ ቲዎሪ ማብራሪያ መሰረት በዚህ ጥናት ውስጥ ከዋኔን ማለት በሰባት ቤት ጉራጌ ውስጥ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የሚቀርቡበት ስልትና ቃል-ግጥሞቹ በሚቀርቡበት ጊዜ የሚደረግ አካላዊ እንቅስቃሴን ማለት ነው፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹን ከዋኔ ከመመልከታችን በፊት በሰባት ቤት ውስጥ ሰው ሲሞት የሚደረጉ የለቅሶ ዓይነቶችን ማየት ጉዳዩን ይበልጥ ለመረዳት ያግዛል፡፡

### 4.1 የሰባት ቤት ጉራጌ የለቅሶ ዓይነቶች

የሰባት ቤት ጉራጌ ህዝብ ወገኑ በመሞቱ ምክንያት የተሰማውን ሀዘን ለመግለጽ ከሚጠቀምባቸው ስልቶች አንዱ ሥርዓተ ለቅሶ መከወን ነው፡፡ የሥርዓተ ለቅሶው ከዋኔ ግን የተለያየ ነው፡፡ በሥርዓተ ለቅሶው ከዋኔ ላይ ልዩነት ከሚፈጥሩ ጉዳዮች አንዱ የሟች ማህበራዊ ደረጃ (social status) ነው፡፡ በዚህ መሠረት የብሔረሰቡ ሥርዓተ ለቅሶ በሁለት ይከፈላል፡፡ አንደኛው "የቁም ብኼ" (የቁም ለቅሶ) የሚባል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ "ብኼ" (ለቅሶ) ይባላል፡፡ ሥርዓተ ለቅሶዎቹ በአጭሩ እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

**"የቁም ብኼ"** ፡- "የቁም ብኼ" ማለት በሰባት ቤት ጉራጌ ውስጥ ታዋቂ ሰዎች ሲሞቱ በማህበረሰብ ደረጃ የሚከወን ሥርዓተ ለቅሶ ነው፡፡ ሥርዓተ ለቅሶው "የቁም ብኼ" (የቁም

[11] የከዋኔ ቲዮሪ እንደሚለው በመልከዓ ምድር በተራራቁ ህዝቦችና ባህሎች መካከል የጋራ የሆኑ እሴቶችና ኪናዊ ባህርያት በመኖራቸው ምክንያት ተመሳሳይ የጥናት ስልቶችም አሉ (Okpewho 1992:7፤ ፈቃደ 1991:34-35)፡፡ ተመሳስሎዎቹ የቋንቋና የባህል ልዩነቶችን የሚሻገሩ በመሆናቸው ምክንያት ለየትኛውም የባህል ጥናት የሚያገለግሉ ተመሳሳይ እሳቤዎች፣ የአጠናንና የአተናተን ስልቶች አሉ፡፡ እነዚህን ስልቶች በመጠቀም ጥናቶችን ማካሔድ በቃል-ግጥም ጥናትና ምርምር የተለመደ ነው (ብርሃኑ 1999:351 ዓ.ም)፡፡ ይህም የቃል-ግጥም ጥናት ባህል-ውሱን ቢሆንም ከሌሎች ባህሎች ውስጥ ከሚካሔድ ጥናት ጋር የሚያመሳስሉት የጋራ ነገሮች መኖራቸውን ያመለክታል፡፡

ለቅሶ) የተባለው ማህበረሰቡ ቆሞ የሚከውነውና በቃል-ግጥሞች የታጀበ በመሆኑ ነው፡፡ "የቁም ብኜ" ማህበራዊ ደረጃን (Social Status) መሰረት አድርጎ የሚከወን በመሆኑ በለቅሶው ላይ የሚከወኑ ቃል-ግጥሞች ሟች በህይወት በነበረበት ወቅት የነበረውን ባህሪ ለመግለጽ የሚገጠሙ ናቸው፡፡ በዚህም ሳቢያ ይዘታቸው የተለያየ ይሆናል፡፡ በግብርና፣ በታታሪነታቸው፣ በታጋሽነታቸው፣ በለጋስነታቸው፣ በጀግንነታቸው፣ በኃይለኝነታቸው፣ በፍርድ አዋቂነታቸውና በአስታራቂነታቸው ለታወቁ ሰዎች የቁም ለቅሶ ይፈጸማል፡፡

**ብኜ፡-** ማንኛውም ሰው ሲሞት የሚደረግ የተለመደ የለቅሶ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ሥርዓተ ለቅሶ ላይ ቃል-ግጥም አይከወንም፡፡ በእርግጥ የማንኛውም ሰው ሞት ቢሆን ለቤተሰቦቹና ለዘመዶቹ ሀዘን ነው፡፡ በዚህም ጊዜ የሟች ቤተሰቦች በተለይም ሴቶች (ልጆቹ፣ ሚስት፣ እናት፣ እህት) ሙሾ መደርደራቸው የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ቃል-ግጥሞች ማህበረሰቡን የሚያሳትፍ የለቅሶ ሥርዓት አይከወኑም፡፡ የሰባት ቤት ጉራጌ የለቅሶ ዓይነቶችንና ለማን እንደሚከወኑ አይተናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለስመ ጥር ወንዶች የሚደረግ የቁም ለቅሶ ክዋኔ እናያለን፡፡

## 4.2 የሰባት ቤት ጉራጌ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክዋኔ

ሰባት ቤት ጉራጌ ውስጥ በመልካም ተግባራቸውና ምግባራቸው የታወቁ ወንዶች ሲሞቱ ህዝቡ አደባባይ ወጥቶ ቆሞ ያለቅስላቸዋል፡፡ አንድ ሰው ሲሞት በማህበረሰቡ የሚከወነው "የቁም ብኜ" የሚገባው መሆን አለመሆኑ የሚወሰነው በማህበረሰቡ በጋራ ሲሆን ሟች በህይወት በነበረበት ወቅት የፈጸማቸው ተግባራት በመመዘን የሚወሰን ነው፡፡ ሟች በአካባቢው የታወቀ መልካም ምግባርና ተግባር የነበረው ከሆነ በመኖሪያ ቤቱና በዋና መንገድ (ጀፎረ) ላይ "ወርኸ" (ምሽግ/ ወሰን) የሚባለውን የተለየ ሥርዓተ ለቅሶ ዜማ ባለው ቃል-ግጥም እና በከበሮ ታጅቦ ይከወንለታል፡፡

ታዋቂ ሰዎች ሲሞቱ ቃል-ግጥም የመደርደር ክህሎት ያላቸው አስለቃሾች ተፈልገው ሥርዓተ ለቅሶውን እንዲመሩት ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ለአጋዝ ህትት የተከወነው የቁም ለቅሶ በዋናነት የመሩት የወንድማቸው ልጅ ደምስስ ኤግነት ነበሩ፡፡ ሌላው ለቀስተኛ እነርሱን ተከትሎ ሥርዓተ ለቅሶውን ከውኗል፡፡ አስለቃሹ የተመረጡት የሟችን ዘር፣ ገድልና ዝና የሚያውቁና ይህንኑ መግለጽ የሚችሉ በመሆናቸው ሲሆን ይህንኑ የሚያወሱ ቃል-ግጥሞችን አሰምተዋል፡፡ የቃል-ግጥሞች ይዘት እንደ ሟቹ ተግባር የተለያየ ቢሆንም የ"ቁም ብኜ" ክዋኔ ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን የቁም ለቅሶ በሚከወንበት ጊዜ ወንዶችና ሴቶች የሚሳተፉት በተለያየ መንገድ ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ማብራሪያ በአጋዝ ህትት ላጫ ለቅሶ ላይ የተከወነ ነው፡፡

ወንዶች ለቅሶ ለመድረስ የመጡት በእግርና በፈረስ ነበር፡፡ በፈረስ የመጡ ወንድ ለቀስተኞች በፈረሶቻቸው ላይ ሆነው ከሟች ቤት ፊት ለፊት በሚገኝ በዋና መንገድ (ጀፎረ) ላይ ፈረሶቻቸውን እየጋለቡ የሟችን ተግባር ያወሱ ነበር፡፡ በእግር የመጡ ወንዶች ደግሞ ከዘራቸውን ከሟች ቤት ደጃፍ መሬት ላይ በማጋደም ቀድሞ ከመጣው ቀስተኛ ጋር ይቀላቀላሉ፡፡

በተጨማሪም አዋቂ ወንዶች የሃዘናቸውን ጥልቀት ለመግለጽ ጀርባቸውን በአለንጋ እየገረፉ፤ ጎናቸውን ደግሞ በክርናቸው ይጎስሙ ነበር፡፡ በአለንጋ ሰውነትን መግረፍና በክርን ጎንን መጎሰም በአልቃሹና በሟች መካከል ያለውን የግንኙነት ሁኔታ ያመለክታል፡፡ የግርፊያው ወይም የጉሰማው ጥንካሬ በሟችና በአልቃሹ መካከል እንዳለው ዝምድና ወይም የቅርበት መጠን የተለያየ ነው፡፡

የሟች የቅርብ ዘመድ የሆኑ ወንዶች የሟችን ፈረስ በለቀስተኛው መሃል እየጎተቱ በመዘዋወር ሟችን እያወሱ ያለቅሱ ነበር፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንዳሉት ሟች ይጠቀምባቸው የነበሩ ቁሳቁሶችን ይዞ ማልቀስ የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ በጀግንነቱ የታወቀ ሰው ሲሞት ጦር፣ ጎራዴ፣ ጋሻ፣ ጠብመንጃና ሌሎችም መሳሪያዎችን በመያዝና የነብር፣ የአነርና የጉሬዛ ቆዳ (ለምድ) በመልበስ በቁም ለቅሶ ላይ መሳተፍ የተለመደ ነበር (ደምስስ ኤግነት፣ አዝልቄ ሲማ)፡፡

ወጣት ወንዶች ራሳቸውን በሁለት እጆቻቸው በመያዝ ጎንበስ ቀና እያሉ አልቅሰዋል፡፡ በአለንጋ ሰውነትን የመግረፍና በክርን ጎንን የመጎሰም ሁኔታ በወጣቶች ዘንድ እምብዛም አይታይም፡፡ አዋቂዎችን ተከትለው ለቀስተኛውን ይቀላቀላሉ፡፡ በፈረስም ይሁን በእግር የመጡ ወንድ ለቀስተኞች ከሴቶቹ ቀድመው ወደ ለቅሶው ቤት/ግቢ ይገባሉ፡፡ ሴቶች ከኋላ ይከተላሉ፡፡ ወንድና ሴት ፊትና ኋላ ሆነው እንጂ አንድ ላይ ሆነው ለቅሶ አይገቡም፡፡ ከገቡ በኋላም የተቀመጡት ለየብቻ ነበር፡፡

እንደ ወንዶች ሁሉ ሴቶችም ሀዘናቸውን የሚገልጹት በልዩ ልዩ ክዋኔ ነው፡፡ የሟች የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሴቶች ከፍ እያሉ ይዘሉና መሬት ላይ በታፋቸው በመፈጥፈጥ ሀዘናቸውን ገልጸዋል፡ ፡ አጠንክሮ ወይም አቅልሎ ደረት በመደቃትና መሬት ላይ በኃይል ወይም በቀላሉ በመፈጥፈጥ የሚገለጽ ሀዘን በአልቃሿና በሟች መካከል ያለውን ዝምድና ወይም ቅርበት ያመለክታል፡፡ የሟች የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሴቶች ሟች ሲጠቀምባቸው የነበሩ አልባሳቶችን ለምሳሌ ጭራ፣ አለንጋ፣ ባርኔጣ፣ ካፖርትና ሱሪና ይዘው ለቀስተኛው እንዲመለከት ከፍ አድርገው በመያዝ አልቅሰዋል፡፡

ሴቶች እጆቻቸውን ግራና ቀኝ ዘርግተው፤ የእጆቻቸውን አንጓ በማጠፍ ጣቶቻቸውን አንዴ ወደ ፊት፣ አንዴ ወደ ኋላ፤ አንዴ ደግሞ ወደ ላይና ወደ ታች ስልት ባለው ሁኔታ ያወዛውዙ ነበር፡፡ አየሩን እየቀዘፉ፣ መሬቱን በእግሮቻቸው ጣቶች በመርገጥ ስልት ባለው እንቅስቃሴ ከፍ እና ዝቅ እያሉና እየተውረገረጉ የመላ አካላቸው እንቅስቃሴ በማስማማት የቁም ለቅሶ በሚከወንበት ቦታ ላይ ወንዶችን መሀል ያደረገ ክብ ሰርተው ይዞሩ ነበር፡፡ የእጆቻቸውና የእግሮቻቸው እንቅስቃሴዎች ተናባቢ ናቸው፡፡ በግብታዊነት የሚንቀሳቀስ የአካላቸው ክፍል አይታይም፡፡ አካላዊ እንቅስቃሴው ሴቶቹ ከሚያሰሙት ለቅሶ ድምጽ እና እንቅስቃሴ ጋር በሚስማማ ስልት ይከወናል ነበር፡፡ ክዋኔያቸው በታዳሚው ላይ ጥልቅ ሆነ የሀዘን ስሜት የመፍጠር ኃይል አለው።

ደረታቸውን የሚደቁም ነበሩ፡፡ የሴቶቹ እንቅስቃሴ ከከበሮው ምትና ከወንዶቹ ክዋኔና እንቅስቃሴ ጋር በሚናበብ ሁኔታ ይከወን ነበር፡፡




ስዕል 2. የቁም ለቅሶ (ወርኮ)፣ የካቲት 2008 (የግንድ፣ ጉመር)፣ ሴቶች

የቁም ለቅሶው *ሥነ-ሥርዓት* ክዋኔ በከበሮ የታጀበ ነበር፡፡ ከበሮውን ሲመቱ የነበሩት ሴቶች ናቸው፡፡ የለቅሶ *ሥርዓቱ* የተከናወነው ከበሮ የሚመቱ ሴቶችን ማዕከል ያደረገ ክብ በመስራት ነበር፡፡ ክቡ ሦስት ቀለበቶች ነበሩት፡፡ የመጀመሪው ክብ ላይ የነበሩት ወንዶች ናቸው፡፡ ወንዶች በሁለት ቡድን በመሆን ከበሮ የሚመቱትን ሴቶች መሀል አድርገው ቆመው ኢጋዝ ሀትትን የሚገልጹ ቃል-ግጥሞችን ዜማ ባለው ድምጽ እየተቀባበሉ ያሰሙ ነበር፡፡ ቀስ እያሉም ክቡን ሳያፈርሱና አንዱ ቡድንም ከሌላው ጋር ሳይደባለቅ ይዞሩ ነበር፡፡ የሚዞሩትም የሰዓት ቆጣሪ ከሚዞርበት አቅጣጫ በተቃራኒ ነበር፡፡ ወንዶች ሲያሰሙት የነበረው ድምጽና ሲያደርጉት የነበረው የአካል እንቅስቃሴ ከከበሮው ምት ጋር የሚናበብ ነበር፡፡

ከወንዶች ቀጥሎ የተፈጠረው ሁለተኛውን ክብ የሰሩት ሴቶች ናቸው፡፡ ሴቶቹ ወንድ ለቀስተኞችን መሀል የሚያስገባ ክብ ይሰሩና ከወንዶቹ በውጭ በኩል የክቡን መስመር ተከትለው እየዞሩ አልቅሰዋል፡፡ በዚህም ጊዜ ሴቶቹ ከወንዶቹ ጋር አይደባለቁም፡፡ ሦስተኛውን ክብ የሰሩት ደግሞ በዳር በኩል አመቺ በሆነ ቦታ ላይ ቆመው/ተቀምጠው ክዋኔውን ሲመለከቱ የነበሩ ለቀስተኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖች ጃንጥላ ዘርግተውና በዛፍ ጥላ ስር ሆነው ይከታተሉ ነበር፡፡ ሰዎቹ በቁም ለቅሶው ክዋኔ ላይ ባይሳተፉም *ሥርዐተ* ለቅሶው በሚፈጸምበት ቦታ ነበሩ፡፡ ከሁሉም *ፆታ* የነበሩ ወጣቶች፣ አረጋዊያን፣ በሃይማኖታቸው ምክንያት[12] የቁም ለቅሶ መከወን የማይችሉ ለቀስተኞች በዚህ ክብ ላይ ቆመው እንደነበሩ ተመልክቻለሁ፡፡ አልባሳትን በተመለከተ ግን ለለቅሶ ተብሎ የሚለበስ የተለየ የአለባበስ ሁኔታ አልነበረም፡፡ ለቀስተኛው ያለውን ልብስ ለብሶ እንደሚመጣ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ፡፡ በኢጋዝ ሀትት ለቅሶ ላይ የተገኙት አብዛኛዎቹ

[12] የእስልምናና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በቁም ለቅሶ ላይ ሲሳተፉ አይታዩም (አበጋዝ ደዊ ቤዛ፣ ለጃ አህመዴ)፡፡

ወንዶች ከላይ ካፖርት ደርበው ነበር፤ ኮፍያ (ባርሜጣ) አድርገዋል፤ አብዛኛዎቹ ሽመል ከዘራ ይዘው ነበር፡፡ ሁሉም ሴቶች ከላይ ነጠላ ለብሰው ነበር፡፡ ነገር ግን በከተሞች አካባቢ እንደምናውቀው ዓይነት ነጠላ ዘቅዝቀው የለበሱ የገጠር ሴቶች አላየሁም፡፡



ስዕል 3. የቁም ለቅሶ፣ የካቲት 2008 (የግንድ፣ ጉመር)

ለአጋዝ ሀትት ከተገጠሙ ቃል-ግጥሞች መካከል ለአብነት ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

**ጀግንነታቸውና ኃይለኝነታቸው የሚገልጹ**

| ጉራጌኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ ምሽጉ |
| የላጫ ኤገዋረ | የላጫ [ልጅ] ልበ ሙሉ |
| ቦገት ኻመመረ | በአደባባይ አስገመገመ |
| ብርጫሟኸ | አንተ ልዩ ነህ! |
| | |
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ ምሽጉ |
| የላጫ ኤገዋረ | የላጫ [ልጅ] ልበ ሙሉ |
| ኤነወ ውዝግፐረ | ፀፀት የለበትም |
| ብርጫሟኸ | አንተ ልዩ ነህ! |
| | |
| ኦኦኦ...ሆ..ሆ..ሆ | ኦኦኦ...ሆ..ሆ..ሆ |
| የኸሸ አዊ | ይኸው አውሬው |
| ኦ! አዊ | አዎን አውሬው |
| ያንበሳ ሞሳ | የአንበሳው ልጅ [ደቦል] |
| ገግመታ አንበሳ | ራሱም አንበሳ ነበር |
| ዞቢ፡፡ | ዳርቻ [ድንበር]፡፡ |

| | |
|---|---|
| ወርኮ ተባነረ ወርኮ | ምሽጉ ተናደ መሽጉ |
| አዊ ስማ አዊ | አውሬው ስማ አውሬው [የምታስፈራው] |
| የፋራኽ ድንዴ ዞቤ | የታጋሽ ድችራ ዳርቻ [ድንበር] |
| የብርጫማኽ! | አንተ ልዩ ነህ! |

**ለጋስነታቸውና ቸርነታቸው የሚገልጹ**

| ጉራጌኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ ምሽጉ |
| ዋቢ የረፐረ | ቸር የነበርከው |
| ዋቢ አማከረ | ቸሩ አኮረፈን |
| ብርጫሟኽ | አንተ ልዩ ነህ! |
| | |
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ ምሽጉ |
| የሴፈሆን ወረ | የሰፋኸው ነገረ |
| የሟን አቴግኹረ | ለማን አደራ ሰጠኸው |
| ብርጫሟኽ | አንተ ልዩ ነህ! |
| | |
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ ምሽጉ |
| ዜጋ የበከረ | ለተቸገረ ድሀ |
| ሳጢን ከፎተረም | ሳጥን ከፈተለት |
| ብርጫሟኽ | አንተ ልዩ ነህ! |
| | |
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ ምሽጉ |
| ቲውን የረፐረ | ስትሰጠው የነበረ |
| የሟን አቴግሆረ | ለማን አደራ አልከው |
| የብርጫሟኽ | አንተ ልዩ ነህ! |

**የዳኝነት ችሎታቸውንና አስተዋይነታቸውን የሚገልጹ**

| ጉራጌኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ ምሽጉ |
| ሻካች የረፐረ | አስታራቂ የነበረው |
| ሻካች አማከረ | አስታራቂው ተቀየመ |
| የብርጫማኽ | አንተ ልዩ ነህ! |
| | |
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ሽጉ ተናደ |
| የዘንጋ ሞነ | የነገር ቋት |
| ቁልፈታ ቀነ | ቁልፉ ጠፋ |
| አጅሬ ፎታንም ቸነ | አጅሬ ፈትቶት መጣ |
| የብርጫማኽ | አንተ ልዩ ነህ! |

| | |
|---|---|
| አአሆሆ አአአአ ሆሆሆ | አአሆሆ አአአአ ሆሆሆ |
| ኤረውሪ ኼቶ | በብልሀት አይኖርም |
| ኤረሀዊ ሴቶ | ተፈልጎ አይገኝም |
| ተዳሰም ወጨጫ ቆቶ | የወጨጫ ተራራ ተናደ |
| የብርጫሟኽ | አንተ ልዩ ነህ!! |

**ትጉህ ሠራተኛ እንደነበሩ የሚገልጹ**

| ጉራጌኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ |
| በነን በተት ጎረ | በላይኛውና በታችው እርሻ |
| ቾተም ሸነን ወረም | ሰርቶ በለጸገ |
| የብርጫማኽ | አንተ ልዩ ነህ! |
| | |
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ |
| በሸዋ ተዠንቦረ[13] | በሸዋና በጀምቦሮ |
| ቾተም ሸነን ወረም | ሰርቶ በለጸገ |
| የብርጫማኽ | አንተ ልዩ ነህ! |
| | |
| ወርኮ ተባነረም ወርኮ | ምሽጉ ተናደ |
| አ ደቼ አቦ ደቼ | አ ደቼ አቦ ደቼ |
| ያፈር ዜማገቻ | መሬትን የሚጠብቀው |
| ኧኳ ቦቼ | ዛሬ ተወሰደ |
| የብርጫሟኽ | አንተ ልዩ ነህ! |

## 5. የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ማህበራዊ ፋይዳ

በለቅሶ ላይ የሚከወኑ ቃል-ግጥሞች ልዩ ልዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች አሏቸው፡፡ በዚህ ጥናትም ቃል-ግጥሞች ማህበራዊ ፋይዳ የተተነተነው Malinowsky እና Radcliffe-Brown ተግባራዊነት (Functionalism)[14] ብለው ከሚጠሩት ጽንሰ ሀሳብ[15] አኳያ ነው፡፡ ጽንሰ ሀሳቡ የሚያጠነጥነው

[13] አብዛኛው የገጠሩ ጉራጌ አዲስ አበባን "ሸዋ" ብሎ ነው የሚጠራው፡፡ የዠንቦረ ደግሞ በዚያው አካባቢ የሚገኝ የአነስተኛ ከተማ ስም ነው፡፡

[14] Functionalism የሚለውን እሳቤ የተገኘው ከ Durkheim እንደሆነ ተጽፏል (Radcliffe-Brown 1952:181)፡፡ ፋይዳ በማህበራዊ መዋቅር (Social Structure) ውስጥ ብቻ የሚያገለግል እሳቤ አድርጎ ስለሚበይነው ይህ እሳቤ መዋቅራዊ-ተግባራዊ (Structural Functionalism) ቲዮሪ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ተግባር በአንድ ቡድን አባላት መካከል ያሉ ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚመለከት፣ ቡድኖች ተለይተው የሚታወቁበትን ውስጣዊ መዋቅርና ባህሪ ለመቆጣጠር የሚያግዝ የታወቀ ማህበራዊ ግንኙነት ስልት ነው፡፡

[15] ይህን ጽንሰ ሀሳብ በሚመለከት ሰፊ ማብራሪያ ካቀረቡ ምሁራን መካከል Radcliffe-Brown ዋነኛው ናቸው፡፡ Radcliffe-Brown ተግባራዊ ቲዮሪን ያብራሩት ውስጠ-አካላዊ ሞዴልን (Organismic Model) መሰረት አድርገው

አንድ ባህላዊ ክዋኔ ለሚከውነው ማህበረሰብ ማህበራዊ አገልግሎት ይሰጣል በሚለው እሳቤ ላይ ነው (Okpewho 1992:172-174)፡፡ በዚህ እሳቤ መሰረት የአንድ ማህበረሰብ አባላት የሚፈፅሙት አንድ ባህላዊ ክዋኔ የማህበረሰቡን ደህንነት ለማጠናከርና ህልውናውን ጠብቆ ለማቆየት የሚያስችሉ ማህበራዊ ፋይዳዎች እንዳሉት እንረዳለን፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በአንድ ማህበረሰብ አባላት የሚከወኑ ባህላዊ ተግባራት ለማህበረሰቡ ወይም ለቡድኑ ጠቃሚና አስፈላጊ አገልግሎት ይሰጣሉ ከሚለው ሀሳብ በመነሳት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ጠቃሚ ማህበራዊ ፋይዳ እንዳላቸውና ብሔረሰቡም ቃል-ግጥሞችን የሚከውነው ጥቅም ስለሚሰጡት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በመሆኑም የለቅሶ ቃል-ግጥሞች በዋናነት የብሔረሰቡን የሀዘን መግለጫ ሥርዓት በመግለጽ መልካም ባህሪን ያስተምራሉ፤ ቸርነትን፣ ጀግንነትን፣ ፍትሀዊነትን ያወድሳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምስጉን ባህሪ ያላቸው ወንዶች በብሔረሰቡ ዘንድ ልዩ ክብር የሚሰጣቸው መሆኑን በማመልከት ምግባረ ሰናይነትን የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ የቃል-ግጥሞቹ ማህበራዊ ፋይዳ ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች አንጻር ተተንትነዋል፡፡

### 5.1 ሀዘንን መግለጽና ሀዘንተኛን ማጽናናት

ከለቅሶ ቃል-ግጥሞች ማህበራዊ ፋይዳዎች አንዱ በመልካም ምግባራቸው የታወቁ ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ህዝቡ ለሟች ወገኖቹ ያለውን ክብርና የተሰማውን ሀዘን ለመግለጽ የሚያገለግሉ መሆናቸው ነው፡፡ ህዝቡ ይህን የሚያደርገው የቁም ለቅሶ የሚባለውን የለቅሶ ዓይነት በመከወን ነው፡፡ ለቀስተኞቹ ከምግብና ከመጠጥ በመከልከል፣ አደባባይ ላይ ለረጅም ሰዓት በመቆምና የሟችን መልካም ምግባር ለመግለጽ ቃል-ግጥሞችን ይከውናል፡፡ የተሰማቸውን ሀዘን ይገልጻሉ፡፡

ሀዘንን ከመግለጽ በተጨማሪም ቃል-ግጥሞች የሟችን ቤተሰብ፣ ዘመድና ወዳጆችን የማጽናናት ፋይዳ አላቸው፡፡ ሟች በህይወት በነበረበት ወቅት በማህበረሰቡ ዘንድ የነበረውን ተቀባይነትና ከበሬታ በመግለጽ ማህበረሰቡ የሟችን ቤተሰብ ያጽናናባቸዋል፤ ያለውንም አጋርነት ይገልጽባቸዋል፡፡ እንደዚሁም ቃል-ግጥሞቹ ዜማ ባለው ስልት የሚከወኑ በመሆናቸው በሀዘንና በትካዜ የደከመን አእምሮ የማረጋጋት ኃይል አላቸው፡፡

---

ነው፡፡ በሞዴሉ የቀረበው ሀሳብ እንደሚያሳየው አንድ ክዋኔ በተፈጥሮአዊ የስነ- ህይወት ሳይንስ ውስጥ ተግባር (Function) ካለው በተመሳሳይ ሁኔታም በማህበራዊ ሳይንስ ውስጥም ተግባራዊ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ የአንድ ፍጡር መላ አካላት የሚፈጽሟቸው ተግባራት ተደምረው ፍጡሩን ሙሉና ህያው የሚያደርጉት ከሆነ የባህል ክዋኔዎችም ተደምረው የከዋኙን ማህበረሰብ ህልውና ሙሉ ያደርጉታል (Radcliffe-Brown 1935: 394-397)፡፡

### 5.2 ትውልድን ማስተማርና ማነጽ

የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ከዋኔ በአንደበት ሲነገር የሚሰማና በተግባር ሲከወን የሚታይ በመሆኑ የብሔረሰቡን የሀዘን መግለጫ ሥነ-ሥርዓትና ልማድ ያስተምራል፡፡ ብሔረሰቡ ቃል-ግጥሞችን እንዴት፣ ለምንና ለማን እንደሚከውን በተግባር እየከወ ስለሚገልጻቸው አዲሱ ትውልድ ከከዋኔው ጋር የተያያዙ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በማየት ይማራል፡፡ እንደዚሁም ቃል-ግጥሞች ሲቀርቡ በማዳመጥ የሚነገሩበትን ስልት፣ ምክንያትና ትርጓሜያቸው ይማራል፡፡ እንዲሁም በቃል-ግጥሞቹ ውስጥ የሚተላለፈውን ጥበብ፣ የህይወት ፍልስፍና፣ ዓለማዊ ህይወትን የሚመለከቱ ብሔረሰቡ ያዳበራቸውን ሀገር በቀል እውቀቶች፣ መልካም እሳቤዎችና ባህሪያትን ሁሉ ያስተምራሉ፡፡ እነዚህ እሴቶች ከሚተላለፉባቸው የስነ ቃል ዘርፎች መካከል የሆኑት የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ምግባረ ሰናይነትን ያስተምራሉ፤ ትውልድን ያንጻሉ፡፡

ቃል-ግጥሞች ብሔረሰቡ መልካም ምግባር ላላቸው ሰዎች የሚሰጠውን ከፍ ያለ ከበሬታ ያሳያሉ፡፡ በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ የመልካም ምግባር ባለቤት መሆን በህይወት እያሉም ይሁን ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የሚያስከብር መሆኑን ያሳስባሉ፡፡ ቋሚዎች ለማህበረሰባቸው ጠቃሚ የሆኑ ባህሪያት እንዲያጎለብቱና ጠቃሚ የሆነ ተግባር እንዲፈጽሙ ያነሳሳሉ፡፡ ይህን በማድረግ ብሔረሰቡ በመልካም ምግባራቸውና ተግባራቸው ክብር ከሚሰጣቸው ታዋቂ ሰዎች እንደ አንዱ ለመሆን ጥረት እንዲያደርጉ በማነሳሳትና በማነቃቃት ትውልድን ያንጻሉ፡፡

ለምሳሌ በጀግንነታቸው ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ የሚከወኑ ቃል-ግጥሞች የሟችን ጀብዱ የሚያወሱ ናቸው፡፡ በዚህም ታሪክን ይተርካሉ፡፡ እነዚህ ቃል-ግጥሞች ለህዝባቸው ሲሉ በጀግንነትና በድፍረት አደጋን የተጋፈጡ የጀግኖች ታሪክ ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ታሪካዊ ድርጊት ፈፃሚዎችንና ድርጊቱ የተፈፀመባቸውን ሁኔታዎች በመተረክ በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ የጀግናን ወኔ ያሰርጻሉ፡፡ በዚህም የህዝባቸውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ድፍረት፣ ጀግንነትና ወኔ ያለው ትውልድ ለማነጽ ያገለግላሉ፡፡

### 5.3 ማወደስና መንቀፍ

ከለቅሶ ቃል-ግጥሞች ማህበራዊ ፋይዳ መካከል አንዱ ውዳሴ ነው፡፡ የተለያዩ መልካም ተግባራትን የፈጸሙ ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ያወድሳል፡፡ በግጥሞቹ የሚወደሰው ርዕሰ ጉዳይ ግን እንደ ሟች ምግባር የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ በአጋዝ ህትት ለቅሶ ላይ የተከወኑ ቃል-ግጥሞች የሟችን ጀግንነት፣ ትጉህነት፣ ሊጋስነት፣ ብልህነት፣ ወዘተ የሚያወድሱ ነበሩ፡፡

በመልካም ምግባራቸው የታወቁ ሰዎች ሲሞቱ የሚከወኑ ቃል-ግጥሞች ምግባረ ሰናይነትን የሚያወድሱ ናቸው፡፡ በባህላችን ሰው በሞተ ጊዜ ስለ ማይወቀስ ሰነፍ፣ ፈሪ፣ ንፉግ፣ ኢ-ፍትሀዊ ወዘተ የሆነ ሰው በዚህ ምግባሩ አይወቀስም፡፡ በመሆኑም ትጉ፣ ጀግና፣ ቸር፣ ለነበሩ ሰዎች ክብር በመስጠትና በማወደስ ምግባረ ብልሹነትን ይነቅፋል፡፡ ለምሳሌ ጀግኖችን የሚያወድሱ ቃል-

ግጥሞች ዜማዊ በመሆናቸው ፈሪነትን የሚነቀፍባቸው ናቸው፡፡ ፍትሀዊነትን በማወደስ ኢ-ፍትሀዊነትን ይነቅፋሉ፣ ታታሪነትን በማወደስ ስንፍናን ይነቅፋሉ፡፡ በመሆኑም በብሔረሰቡ ዘንድ ስንፍና፣ ጦርነት፣ ስርቆትት፣ ውሸታምነትና የመሳሰሉት ባህሪያት እንዳይስፋፉና መልካም ባህሪያት እንዲጎለብቱ የማድረግ ፋይዳ አላቸው፡፡

### 5.4 የብሔረሰቡን ባህል መጠበቅና ማስተላለፍ

የጉራጌ ብሔረሰብ ባህሉን ጠብቆ ከሚያቆይባቸውና ከሚያስተላልፍባቸው የስነ-ቃል ዘርፎች አንዱ ቃል-ግጥም ነው፡፡ ቃል-ግጥሞቹ የብሔረሰቡን የህይወት ፍልስፍና የሚገልጹ እንዲሁም ሀዘን፣ ጀግንነት፣ የሥራ ወዳድነት፣ ደግነት፣ ታጋሽነትና ታሪክ የሚያወሱ በመሆናቸው ብሔረሰቡ ለሟች ዘመዱ ያለውን ከበሬታና በሞቱ የተሰማውን ሀዘን ይገልጽባቸዋል፡፡ ብሔረሰቡ የሟች ቤተሰቦችን የሚያጽናናበት ሥርዓትና እውቀት የያዙ በመሆናቸው የሀገር በቀል እውቀት ማህደር ናቸው፡፡ ቃል-ግጥሞቹ ብሔረሰቡ እውቀቱን ከሚገለጽባቸው፣ ጠብቆ ከሚያቆይባቸውና ከሚያስተላልፍባቸው ስልቶች አንዱ ናቸው፡፡

የቃል-ግጥሞቹ ክዋኔ ሀገር በቀል እውቀት ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ የሚተላለፍበት መንገድ ነው፡፡ ሥርዓቱ ወደ ሌላው ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ ቃል-ግጥሞቹ ህዝቡ ያዳበረውን እውቀት በአንደበትና በድርጊት ተጠብቆ እንዲቆይና ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ከሚያደርጉ ሀገር በቀል እውቀቶች አንዱ በመሆናቸው ላቅ ያለ ፋይዳ አላቸው፡፡ ማህበረሰቡ ያሳለፈውን የህይወት ውጣ ውረድ የሚዳስሱና ግንዛቤ የሚያስጨብጡ በመሆናቸው መልካም እሴቶች ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ በቃል አማካይነት እንዲሸጋገር ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም እንደ ቃላዊ ጥበብነታቸው በብሔረሰቡ ታሪክ ውስጥ ገናና የነበሩ ጀግኖችን ታሪክ እያወሱ ልዩ ልዩ እሴቶችን በማስተላለፍና ቀጣይነት እንዲኖራቸው በማድረግ ማህበረሰቡን ያገለግላሉ፡፡

ቃል-ግጥሞቹ ከፍ ያለ ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው ቢሆኑም ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳቸው ለለውጥ የተጋለጠ ነው፡፡ በመሆኑም በቃል-ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ላይ የሚታየው ለውጥና ቀጣይነት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 6. የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ለውጥና ቀጣይነት

### 6.1. የቃል-ግጥሞች ክዋኔ ለውጥ

ስነ-ቃል ሕያው ባህል ተብሎ የሚጠራው በቋሚነት ያለና አዲስ የሚፈጠርም በመሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በቃል-ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ላይ የሚታየው ለውጥና ቀጣይነት ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች አሉት፡፡ አንድ ህዝብ በራሱ ውስጥ በሚፈጠር ለውጥና ከሌላ ህዝብ ጋር በሚያደርገው ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ሳቢያ የሚመጡ ለውጦች ይኖራሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የለቅሶ ቃል-ግጥሞችንም የሚያካትት ሲሆን ከወቅቱ

ፍላጎትና አስተሳሰብ ጋር አብረው የማይሔዱት እየጠፉ በሌላ ይተካሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ተጠብቀውና ዘመን ተሻግረው ይቀጥላሉ፡፡ በሰባት ቤት ጉራጌ የቃል-ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ለውጥ የሚያስከትሉ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### 6.1.1 የለቅሶ ቃል-ግጥሞቹ ባህሪ

የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ከተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ለሚመነጩና ለውጦች የተጋለጡ ናቸው፡፡ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ከሞትና ከሀዘን ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ክዋኔው (ድርጊቱ) ሁልጊዜ የሚፈጸምና የሚደመጥ አይደለም፡፡ ሰው በተፈጥሮው ተመልሶ ሊያስታውሳቸው ከማይፈልጋቸው መጥፎ ትውስታዎች (bad memories) ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ከተፈጥሯዊ ዐውዳቸው ውጭ የሚከወኑ አይደሉም፡፡ ይህ ሁኔታ ለልዩ ልዩ ውስጣዊና ውጫዊ ተፅዕኖዎች የተጋለጡ ስለሚያደርጋቸው ክዋኔና ፋይዳቸውም እንዲሁ ለለውጥ የተጋለጠ ነው፡፡

### 6.1.2 የቃል-ግጥሞች ክዋኔና ፋይዳ የሚያውቁ አዛውንቶች መመናመን

የለቅሶ ቃል-ግጥሞችን ክዋኔና ፋይዳ የሚያውቁ አዛውንቶች ቁጥር በመመናመን ላይ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም የብሔረሰቡ ቋንቋ የጽሁፍ ቋንቋ ስላልሆነ ብሔረሰቡ እውቀቱን፣ ልማዱንና ወጉን ጠብቆ ያቆየውና የሚያስተላልፈው በቃል እንጂ በጽሁፍ ተሰንዶ አይደለም፡፡ *በቃል ያለ ይረሳል፤ በጽሁፍ ያለ ይወረሳል* እንደሚባለው ቃል-ግጥሞችን የሚያውቁ አዛውንቶች እውቀታቸው በሚገባ ከመሰነዱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ አለያም በዕድሜ መግፋት የተነሳ ቃል-ግጥሞችን ይረሳሉ (ዘርፉ አንሳ፣ አዝልቄ ሲማ፣ ደዊ ቤዛ)፡፡ ስለ ቃል-ግጥሞች ክዋኔና ፋይዳ የሚያውቁ አዛውንቶች ቁጥር መመናመን ሊኖረን የሚገባውን እውቀት አብሮ ይመናመናል፡፡ ይህ ሁኔታ በቃል-ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ያለው ተፅዕኖ አሉታዊ ነው፡፡ በዚህም ሀገር በቀል እውቀትን ለቀጣይ ትውልድ የሚተላለፍባቸው ባህላዊ ሥርዓቶች አንዱ የሆነው ለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ እየተለወጠ በመሄድ ላይ በመሆኑ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች የመረሳትና የመለወጥ ሥጋት ተጋርጦባቸዋል፡፡

### 6.1.3 የብሔረሰቡ አባላት ፍልሰትና የዘመናዊነት መስፋፋት

የጉራጌ ብሔረሰብ አባላት በሥራና በሌሎችም ምክንያቶች በብዛት ወደ ሌሎች አካባቢዎች ይሔዳሉ፡፡ የብሔረሰቡ አባላት ከተለያዩ ማህበረሰቦች ጋር በሚያካሔዱት የባህል ልውውጦችና የገጠር-ከተማ ፍልሰት ሳቢያ የብሔረሰቡ ባህል በለውጥ ሒደት ላይ ነው፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ የሚደረገው የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ዘመናዊነትን በማስፋፋት አዳዲስ ባህላዊ ፍላጎቶች እንዲፈጠሩና እንዲያድጉ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም የብሔረሰቡን የማንነትና የጋራ አስተሳሰብ መገለጫ የሆኑ ባህላዊ እሴቶች ለተለያዩ ተፅዕኖዎች ተጋላጭ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል የለቅሶ ቃል-ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ አንዱ ነው፡፡

የብሔረሰቡ አባላት በብዛት ወደ ከተሞች መፍለስና የከተማ ነዋሪ ጉራጌዎች ከትውልድ ቀያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ጠብቀው በመቆየታቸው አካባቢው ከከተሞች ጋር ያለው ግንኙነት ጠንካራ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ከተሜዎች ከሚኖሩበት አካባቢ ካለው የለቅሶ ሥርዓትና ልማድ ጋር ስለሚላመዱ ባህላቸውን ጠብቀው ለመቆየትና ለማዳበር ያላቸው እድል አነስተኛ ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደ ተናገሩት ከተሜዎቹ የቀሰሟቸው አዳዲስና ልማዶችንና ባህሎችን ይዘው ስለሚመጡ በብሔረሰቡ የሀዘን መግለጫ ሥነ ሥርዓት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አሉታዊ ነው፡፡ ከተሜወቹ ድርጊት፣ ንግግርና አለባበስ መልካም ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ ሁኔታ የገጠሩ ህዝብ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ከተሜዎችን ለመምሰል ጠንካራ ፍላጎት እንዲያድርበት ያደርጉታል (ተኽልቁ አዋሽ፣ ደምስስ ኤግነት)፣ ይህም ለለውጡ መንስኤ ይሆናል፡፡

በኢጋዝ ህትት ለቅሶ ላይ እንደተመለከትኩት ከከተሞች የመጡ ወንድ ለቀስተኞች አብዛኛዎቹ ከላይ ጋቢ ደርበው ነበር፡፡ የሴቶቹ አለባበስ በከተሞች አካባቢ የተለመደውን ሥርዐት የተከተለ ነበር፤ በዕድሜ ጠና ጠና ያሉት ነጠላ ዘቅዝቀው ለብሰው የነበሩ ሲሆን ጥቁር ሻርፕም የደረቡ ነበሩ፡፡ ከከተሞች የመጡ ለቀስተኞች በቁም ለቅሶው እምብዛም አልተሳተፉም፡፡ ከወንዶቹ መካከል በእድሜ ገፋ ያሉት አልፎ አልፎ ይከውኑ ነበር፡፡ በተጨማሪም የሟችን ፎቶ ግራፍ ይዘው የሚያለቅሱ ቤተሰቦች ነበሩ፡፡ የሟችን "ፎቶ ግራፍ ይዞ የማልቀስ ሁኔታ የብሔረሰቡ አባላት በብዛት ወደ ከተሞች መፍለስ፣ ከከተማ ህይወትና ከፎቶ ግራፍ ጥበብ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመጣ.."(ሙናጃት ተኽልቁ፣ ደምስስ ኤግነት፣ ለጃ አህመዴ)፣ ሆኖ በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ እየታየ ያለውን ለውጥ ያመላክታል፡፡

### 6.2. የቃል-ግጥሞች ቀጣይነት

በቃል-ግጥሞች ክዋኔና ፋይዳ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች ቢኖሩም ተፅዕኖዎች ተቋቁሞ መቀጠል ችለዋል፡፡ ይህም የሆነው ቃል-ግጥሞቹ የሚከወኑት የብሔረሰቡን የለቅሶ ሥርዓት ውስጥ በመሆኑ ነው፡፡ የቃል-ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ቀጣይነት እንዲኖረው ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል ቀጥለው የቀረቡቱ ለምሳሌ ያህል ማንሳት ይቻላል፡፡

**6.2.1** ቃል-ግጥሞቹ የሚከወኑበት ተፈጥሯዊ አጋጣሚ ቀጣይነት ያለው መሆኑ የቃል-ግጥሞችን ክዋኔ ቀጣይነትን ያመላክታል፡፡ የቃል-ግጥም ክዋኔ እንዲቀጥል አስቻይ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱና ዋንኛው ብሔረሰቡ ባህላዊ የሀዘን መግለጫ ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ መቆየቱ ነው፡፡ እንደዚሁም በቁም ለቅሶ ሥርዓት ላይ በሚፈጸሙ ክዋኔዎች ውስጥ የሚያደርገው ተሳትፎ ቀጣይነት ያለው መሆኑ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በጋራ ሆነው ከሚፈጽሟቸው ማህበራዊ ክዋኔዎች አንዱ የቁም ለቅሶ ሥነ ሥርዓት ነው፡፡ በለቅሶ ወቅት የሚፈጸሙ የቃል-ግጥም ክዋኔዎች የብሔረሰቡን የሀዘን መግለጫ ሥርዓት ጠብቆ ለማቆየትና ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ አስፈላጊ መሆናቸው ቀጣይነታቸውን አመላካች ነው፡፡

**6.2.2** የየዘመኑን ፍላጎት መሰረት አድርጎ የሚከወኑ የለቅሶ ቃል-ግጥሞች አሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚገጠሙ ቃል-ግጥሞች ይዘታቸው እንደ ሟቹ ገድልና እንደ ዘመኑ ፍላጎት የተለያየ ቢሆንም

የሚከወኑት ግን የብሔረሰቡን የቁም ለቅሶ አከዋወን ሥርዓት መሰረት መሆኑ የ ቃል-ግጥሞቹ ቀጣይነት ያሳያል፡፡

**6.3 ይሁንታ**

**6.3.1** ብሔረሰቡ ከሞትና ከህይወት ጋር ተያይዞ ያለውን እውቀት ጠብቆ የሚያቆይባቸውና የሚያስተላልፍባቸው ስኬታማና ባህላዊ ስልቶችን በትክክል ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ጠንካራ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚከናወንበት ሁኔታ መፍጠር፣

**6.3.2** የቃል-ግጥሞን ከዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ ከመረሳትና ከመጥፋት ለመታደግ አሁን በህይወት ከሚገኙ ታዋቂ ከዋኞችና አዛውንቶች መረጃዎችን ሳይንሳዊ በሆነ የጥናት ዘዴ ማጥናትና መሰነድ፣

**6.3.3** የብሔረሰቡ አባላት በብዛት ወደ ከተሞች መፍለስና የከተማ ነዋሪዎች ከትውልድ ቀያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ጠብቀው በመቆየታቸው አካባቢው ከከተሞች ጋር ያለው ግንኙነት ጠንካራ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በዚህም የተነሳ ከተሜዎቹ የቀሰሟቸው አዳዲስ ሥርዓትና ልማዶች ወደ አካባቢው ለመስፋፋት ሰፊ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ በከተሞች አካባቢ የተለመደው ሥርዓት በብሔረሰቡ ባህል ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ የገጠሩ ህዝብ በተለይም ወጣቱ ትውልድ የከተሜዎችን ተግባር ለመቅዳትና አስመስሎ ለመተግበር ጥረት ያደርጋል፡፡ ከተሜዎቹ ወደ አገር ቤት የሚመለሱባቸው አጋጣሚዎችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ቢሰራ፣

ይህ የመፍትሔ ሀሳብ የሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ጥረት የሚጠይቅ ቢሆንም ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በዘርፉ የተሰማሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰብ ምሁራን በማስተባበር አጠቃላይ የባህል መነቃቃት በመፍጠር መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና መሰነድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት


ሰይፉ ድባቤ፡፡ 1966፡፡ *አዝማች፡ የጉራጌ ህዝብ አጭር ታሪክ፡፡* አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገ/ስላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

ሰፋ መካ፡፡ 1981፡፡ "የወየግ ዘፈን ግጥሞች"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

በርናል ማርቲን ፡፡1989፡፡ "ጉራጌኛ የግዕዝ አያት ነው" ፤ እፎይታ፡፡ ቅጽ 5፣ ቁጥር 1፣ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ 1999፡፡ *የአማርኛ ሥነግጥም፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዓለማየሁ ነሪ፡፡ 1985፡፡ *ኧሰት ፤ የጉራጌ ባህልና የኢትዮጵያ ማሰረታዊ ታሪክ፡፡* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ወርቁ ንዳ፡፡ 1983፡፡ *ጀብዱ፣ የጉራጌ ባህልና ታሪክ፡፡* አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ቤት፡፡

ወርቁ ወጌ፡፡ 1982፡፡ "የቸሀ ጉራጌ የልደትና የሞት ሥርዓት"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ 1992፡፡ *የስነጽሑፍ ማሰረታውያን፡፡* አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1991)፣ "የቤተ ጉራጌ ምሳሌያዊ ንግግሮች፡፡" አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ደጉ ወ/ጊዮርጊስ፡፡ 1972፡፡ "የጌቶ ብሔረሰብ የሰርግና የልቅሶ ግጥሞች"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ድንበሩ ዓለሙና ሌሎች፡፡ 1987፡፡ *ጎጎት፣ የጉራጌ ብሄረሰብ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ፡፡* ወልቂጤ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ገብረ ዮሐንስ ሜራጋ፡፡ 1964፡፡ "የቸሀ ጉራጌኛ ግጥሞች"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ 1984፡፡ "አፋዊ ኪነተ ቃል" ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ መጽሔት፡፡ ቁጥር 2፡፡

---------፡፡ 1991፡፡ *የሥነ-ቃል መምሪያ፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Bahru Zewde.1972. "The Aymallal Gurage in the Nineteenth Century: A Political History". *Trans African Journal of History*. 2(2).

Barnard, Alan. 2004. *History and Theory in Anthropology.* University of Edinburgh: Cambridge University Press.

Bauman, R. and Joel Sherzer (ed.) .1974. *Explorations in the Ethnography of Speaking*. New York: Cambridge University Press.

Bauman, Richard. 1983."The Field Study of Folklore in Context". In: *Hand Book of American Folklore.* Bloomington.

Ben-Amos, D. 1982. *Folklore in Context: Essays.*New Delhi, Madras: South Asian Publishers.

Ben-Amos, Dan. 1993. "Context in Context." In *Western Folklore*, *Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture.* Vol. 52, No. 2/4, Stable URL.

Berhanu Gebeyehu. 1998. "Islamic Oral Poetry in Wallo. A Preliminary Descriptive Analysis". MA Thesis, School of Graduate Studies: Addis Ababa University.

Borofsky, Robert. 1994. *Assessing Cultural Anthropology*. New York: McGraw-Hill, Inc.

Dorson, M. Richard. 1963. *Current Folklore Theories: Current Anthropology.* Vol.4, No.1.

Dundes, A. 1980. *Essays in Folkloristic*. Delhi: Rajkamal Electric Press.
Erickson, Paul and Liam Murphy. 2008. *A History of Anthropological Theory: 3rd edn*. Canada: Broadview Press.
Fekade Azeze. 1998. *Unheard Voices: Drought, Famin and God in Ethiopian Poetry*. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.
Finnegan, Ruth. 1970. *Oral Literature in Africa*. Nairobi: Oxford University Press.
Finnegan, Ruth. 1992. "Oral Poetry". In Richard Bauman (ed.). *FOLKLORE, CULTURAL PERFORMANCES, AND POPULAR ENTERTAINMENT. A Communications-centered Handbook*. New York, Oxford: Oxford University Press.
Goldestein, Kenneth. 1964. *A GUIDE FOR FIELD WORKERS IN FOLKLORE*. Pennsylvania: Folklore Associates, Inc.
Gurage Development Program (GDP). 1998. "Achievements to Date and Future Plan" a Paper Presented to Country Planning Mission: NP, (unpublished).
IPcar. 1970. "The Gurage Cultural Landscape: A System Interpretation". M.A. Thesis, Michigan State University.
Leslau, Wolf. 1950. *Ethiopic Documents Gurage: Publications in Anthropology*. New York: The Viking Fund Inc.
Leslau, Wolf. 1952."The Influence of Sidamo in the Ethiopia Language of Gurage," *Language*. Vol. 128, No. 1.
Markakis, J. 1966. *Ethiopia Anatomy of A Traditional Polity*. Oxford: Oxford University Press.
Muluneh W/Tsadik. 1994. "Population Pressure, Land Use Change and Patterns of Agricultural Productivity in Ezana Wollene and Chaha 'Weredas': Sebat-Bet Gurage Land". M.A. Thesis in Agricultural Geography, AAU.
Okpewho, Isidore. 1992. *African Oral Literature*. USA: Indiana University Press.
Population Census Commision. Dec 2008. *Summary and Statistical Report of 2007 Population and Housing Census*. Addis Ababa: United Nations Population Fund (UNDF).
Radcliff-Brown, A.R. 1935. "On the Concepts of Function in Social Science". *American Anthropologist*. No. 37.
Radcliffe-Brown, A. 1952. *Structure and Function in Primitive Society*: *Essays and Addresses*. London: Cohen & West Ltd.
Schoemaker H. George (ed.).1990. "The Emergence of Folklore in Everyday life". Bloomington; Indiana: Trickster Press.
Shack, Wiliam and Habte Mariam Marqos. 1974. *Gods and Heroes Oral Traditions of the Gurage of Ethiopia*. Oxford: Clarendon Press.
Shack, Wiliam. 1966. *THE GURAGE: A People of the Enset Culture*. London, New York, Nairobi: Oxford University Press.

Shack, Wiliam. 1968. "The Masqal-Pole: Religious Conflict and Social Change in Gurage Land". Reprinted form *Africa*. Vol. 38, No 4, London: (IES, Miscellanea 5).

Sims, C. Martha and Stephen Martin. 2005. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition*. Lagon: Utah State University Press.

Trimingham, J.S. 1965. *Islam in Ethiopia*. London: Calendar Press.

Turner, Victor. 1977. *The Ritual Process structure and Anti- Structure*. New York: Cornell University Press.

Ulendorf, E. 1950. "Gurage Notes," In: *Africa*. Vol. XX, Vo.4.

Worku Nida (1994). "The Waq Cult of the Gurage," Bahru Zewde (ed.). In: *Proceedings of the Eleventh International Conference of Ethiopia Studies.* Vol. II, Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies, AAU Printing Press.